# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)

ሰኔ ፲፭ ቀን ፪ ሺህ ፯ ዓ. ም

June 22, 2015

## በተቃዋሚዎች ላይ የሚካሄደውን አፈና፤ እመቃና ግድያ ኢሕአፓ(ዴሞክራሲያዊ) በጥብቅ ያወግዛል!

ህወሓት/ኢህአዴግ ከምርጫ 2007 በፊት ጀምሮ ያለማቋረጠ በተቃዋሚዎች ላይ ሲያካሂድ የቆየውን አፈና፣ ማዋከብና ግድያ አሁንም ቀጥሎበታል። ይህ ባህሪው፣ በአሁኑ ሰዓት በተጠናከር መልክ ከመካሄዱ በስተቀር፣ ገና በንጭጩ፣ ከደደቢት ሳይወጣ የተጠናወተው አባዜ ነው። የዚህ ባህሪው መገለጫዎች የራሱን መሠረታዊ እምነት ተከትሎ ከማንም ትዕዛዝ የማይቀበልና በኢትዮጵያዊነቱና በሀገሩ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ የማያወላውል አቋም ያለውን ግለሰብና ድርጅት/ስብስብ ዋና ጠላት አድርጎ ማየቱ ነው። አሁን በመካሄድ ላይ ያለው አፈና፣ እመቀና ግድያ ህወሓት/ኢህአዴግ ከአሁን ቀደምም በስፋት ሲያካሂደው የነበረ ነው።

ሩቅ ሳንሄድና በሺህ የሚቆጠሩ በህወሓት/ኢህአዴግ እመቃና ግድያ ሕይወታቸውን ያጡ ወገኖቻችንን ሳንጨምር የዚህ ሰሞኑን ብቻ ብንመለከት፣ በደብረማርቆስ የሰማያዊ ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪ የነበረውን ወጣት ሣሙኤል አወቀን ሰኔ 8 2007 ዓ.ም ምሽት ማንነታቸውን በደበቁ የፀጥታ ኃይሎች በደረሰበት ከፍተኛ ድብደባ ሕይወቱ አልፏል። በምዕራብ ትግራይም የአረና/መድረክ የድርጅት ጉዳይ ሀላፊ የነበሩት አቶ ታደሰ አብርሃ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በሦስት የፀጥታ ኃይሎች ተደብድበው ተገድለዋል። እንዲሁም የመድረክ የምርጫ አስተባባሪ የነበሩት አቶ ብርሃኑ ረቦ በደቡብ ክልል በሀድያ ዞን በወታደሮች ከመኖርያ ቤታቸው በግዳጅ ተወስደው ከተገደሉ በኋላ አስከሬናቸው ወንዝ ውስጥ ተጥሎ ተገኝቷል። ከዚህ በተጨማሪ በሰሜን ጎንደር በአይከል ከተማ መብታቸን ይከበር፤ ምርጫው ተጭበርብሯል በማለት ሰላማዊ ሰልፍ በወጡ ወገኖቻችን ላይ በተከፈተው ተኩስ ሰባት ሰዎች ሲሞቱ አሥር ሰዎች በፅኑ ቆስለው በህክምና ላይ ይገኛሉ። በጣም በርካታ ዜጎች ከእስር ለማምለጥ ቤት ንብረታቸውን ጥለው ተሰደዋል። ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላም በሺህ በሚቆጠሩ የተቃዋሚ ፓርቲ አባሎች ላይ ወከባና እንግልት መድረሱ እንደቀጠለ ሲሆን ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ደግሞ ለእስራት ተዳርገዋል። እስካሁን ድረስ ከተገለጸው የ“ምርጫ” ውጤት ውስጥ አገዛዙ 442 የፓርላማ ወንበሮች ሙሉ ለሙሉ አሸንፌአለሁ ካለ በኋላ ይህን አይነት አፋናና የግፍ

**P.O.Box 8141**
**Silver Spring, MD 20910**

**P.O.Box 88675**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 202- 241 2078**

**Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

ግድያ ማስፋፋቱ ምንም ዓይነት ተቃውሞን ለማስተናገድ የማይፈቅድ ፍጹም አምባገነን አገዛዝ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው።

ህወሓት/ኢህአዴግ በምርጫ 97 በዝረራ ከተሸነፈ በኋላ በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ጨርሶ ማሸነፍ እንደማይችል ግልፅ ሆኖለታል። ባለፉት ሁለት ምርጫ ተብዬዎች በዓለም ተሰምቶ በማይታወቅና የቀድሞው የደርግ መንግሥት ከራሱ ጋር ብቻ ተወዳድሮ ካስመዘገው ውጤት የበለጠ የሕዝብ ድምጽ አገኘሁኝ ብሏል። እውነታው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንቅሮ እንደተፋው የአደባባይ ሚስጥር ነው። ይህ ሁኔታም ለአገዛዙ ብስጭቱን፣ ተስፋ መቁረጡንና ፍርሀቱን እጥፍ ድርብ አድርጎበታል። ለዚህም ተጠያቂዎቹ ተቃዋሚዎችና የነፃው ፕሬስ አባሎች ናቸው በማለት እነሱን ለማጥፋት ያላደረገውና የማያደርገው ጥረት የለም።

አገዛዙ ለሚፈጽመው ግድያና ጭፍጨፋ ዋናው ምክንያት ከላይ ከተጠቀሰው መሠረታዊ ባህሪው የሚመነጭ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ደግሞ ተስፋ መቁረጥና ፍርሀት ተጨምሮበት ኢ-ሰብአዊና ኢ-ዴሞክራሲያዊ ባህሪውን የበለጠ አጠናክሮ እንዲገፋበት አድርጎታል። የዘነጋው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ እጁን እንደማይሰጥ በታሪክ የተመሰከረለት መሆኑን ነው። ሕዝባችን በታሪኩ አይቶትና ሰምቶት የማያውቀውን የጣልያን መትረየስ፣ መድፍና የመርዝ ጢስ እንደ ዶፍ ሲወርድበት እንኳን እጅ አልሰጠም፣ በትግሉ ቀጠለ እንጂ። እንዲያም ሆኖ አርበኞች እናቶቻችንና አባቶቻችን ጣሊያንን ድባቅ መተው ለቀጣዩ ትውልድና በመላው ዓለም ለሚገኝ ጥቁር ሕዝብ መመኪያ የምትሆን በኅብረቷ የፀናች ኢትዮጵያን ትተውልን አልፈዋል። በአሁኑ ወቅት በዚህች በተረከብናት ኢትዮጵያ ውስጥ ወገናችን በአንድ በኩል በኑሮ ውድነት እየተጠበሰ በሌላ በኩል ደግሞ በወንጀለኛው የገዢ ቡድን የሚደርስበት ግፍና መከራ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ በመሆኑ ዜጎቿን በእኩልነት የምታስተናግድ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት ትግሉን አጠናክሮ ከመቀጠል ሌላ አማራጭ የለውም። ስለዚህም ከእናቶቻችንንና ከአባቶቻችን የወረስነውን የትግል ወኔ የበለጠ አጠናክረን ትግላችንን መቀጠል ይገባል።

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አገዛዙ በንጹሃን ዜጎች ላይ እያደረገ ያለውን ማንኛውንም ጥቃት በጥብቅ እያወገዘ፣ ሕዝብ ለመብቱና ለነፃነቱ በአንድ ላይ እንዲቆምና ትግሉን እንዲቀጥል ወገናዊ ጥሪውን ያቀርባል። ተቃዋሚ ድርጅቶችም በነጠላ መጠቃትን ለመከላከልና የትግሉን ጊዜ ለማሳጠር መለያየትንና በነጠላ መቆምን በማስወገድ የተባበረ ትግል እንዲያደርጉ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) አሁንም በድጋሚ እያሳሰበ የድርሻውን ለማበርከት ዝግጁነቱም ያረጋግጣል። ይህ ትግል የኛ ነው፤ ታሪካዊ ኃላፊነታችን ብቻ ሳይሆን ሀገራዊ ግዳጃችንም ነው።

## የተባበረ የሕዝብ ትግል ምን ጊዜም አቸናፊ ነው!